ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# በትምህርቱ ዘርፍ ልዩ ድጋፍ የሚሹ ክልሎች

**እየሩስ ተስፋዬ**

በኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት ዘርፍ ዝቅተኛ ተጠቃሚ ለነበሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ እንደሚያደርግላቸው በሀገሪቱ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 89/4 ላይ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ስለዚህ እነዚህ ክልሎች አካባቢዎች ከሌሎች ክልሎችና አካባቢዎች ጋር በዕድገት እስኪመጣጠኑ ድረስ የተለየ የመንግሥት ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል፡፡

ለክልሎች ልዩ ድጋፍ የሚያደርግ ቦርድ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ዝቅተኛ ተጠቃሚ የሆኑ ክልሎች አሉ፡፡እነርሱም የአፋር፣ የሶማሌ፣ የቤንሻንጉል ጉምዝ እና ጋምቤላ ክልሎች ናቸው፡፡ በኋላም በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች ክልልና በኦሮሚያ ክልል የሚገኙ አርብቶ አደር አካባቢዎች የድጋፉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በአማራ ክልል የዋግህምራ ዞን ተጠቃሚ ለማድረግ እንቅስቃሴ ተጀምሯል፡፡ ትምህርት ሚኒስቴርም የቦርዱ አባል እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በትምህርት ሥርዓቱ ላይ በጉልህ ከሚታዩ ችግሮች ውስጥ አንዱ የትምህርት ብክነት ነው፡፡ ይህም ማለት ትምህርት ማቋረጥ እና መድገም ሲሆን፣ ችግሩ በስፋት ከላይ በተጠቀሱት ክልሎች ላይ ይስተዋላል፡፡ በእነዚህ ክልሎች ላይ ዛሬም ድረስ በዛፍ ጥላ ሥር እና በዳስ የሚማሩ አልጠፉም፡፡ የትምህርት ተሳትፎ መጠናቸውም በቂ የሚባል ባለመሆኑ ትምህርት ሚኒስቴር ችግሮቹን ለመቅረፍ የተለያዩ ሥራዎችን በመከወን ላይ ነው፡፡

አቶ ፈቃደ ነጋሽ፣ የልዩ ድጋፍና አካቶ ትምህርት ዳይሬክቶሬት ባለሙያ ናቸው፡፡ ሚኒስቴሩ ከትምህርት ዘርፍ ጋር በተያያዘ ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ክልሎች እያከናወነ ያለውን ድጋፍ ሲገልጹ፤ የትምህርት ሥርዓቱ የሚመራበትን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና መመሪያዎችን ለክልሎች ማዘጋጀት፣ የክልሎቹን የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ለማሻሻል አጫጭር ስልጠና መስጠትና ፖሊሲዎች፣ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች በተቀመጠላቸው አቅጣጫ መሠረት መከናወንና አለመከናወናቸውን መከታተል ናቸው፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ መደበኛው የትምህርት አቅርቦት ለአርብቶ አደሩ ተስማሚ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከመስከረም እስከ ሰኔ ያሉ የትምህርት ወራት፣ ከሰኞ እስከ ዓርብ ያለው የትምህርት መስጫ ቀናት እንዲሁም የመማሪያ ጊዜያት ለአርብቶ አደሩ ምቹ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አርብቶ አደሩ ወቅት ጠብቆ ከቦታ ቦታ የሚንቀሳቀስ ማህበረሰብ ስለሆነ ነው፡፡

‹‹በመሆኑም ሥርዓተ ትምህርቱ ከአርብቶ አደሩ የኑሮ ዘይቤ ጋር መጣጣም ይገባዋል፡፡ ነባራዊውን የአርብቶ አደሩ ችግር የሚቀርፍ መሆን ይገባዋል፡፡›› ያሉት ባለሙያው፤ መሠረታዊ ትምህርት የሚሰጥበት፣ ከመደበኛው ትምህርት ጋር እኩል የሆነ የ“አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት” ተግባራዊ እየተደረገ እንደሚገኝም ነግረውናል፡፡ከአንደኛ እስከ አራተኛ ክፍል ጋር የሚመሳሰል ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት የአማራጭ መሠረታዊነት ትምህርት እየተሰጠ ሲሆን፣ አብዛኛዎቹ የሶማሌና የአፋር ክልል ተማሪዎች የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ተማሪዎች ናቸው፡፡

አሁን እየተከናወኑ ካሉ ተግባራት መካከል ሰነድ ተዘጋጅቶ ለመጽደቅ የተወሰነ ሥራ የሚቀራቸው እንደሆነ የሚናገሩት ባለሙያው፣ የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ ከትምህርት ፍኖተ ካርታው ጋር ተስማምቶ ተዘጋጅቷል፡፡ በቅርብ ጊዜ ወደ ክልሎች ይላካል፡፡ የቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያን ወይም ከደረጃ አንድ እስከ ደረጃ አራት ያለው እስከ ደረጃ ስድስት ለማሳደግም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡ የቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያን ወደ መደበኛ ትምህርት ቤት እንዲያድግም መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

በመሻሻል ላይ ከሚገኙት መካከል የአርብቶ አደር ትምህርት ስትራቴጂ አንዱ እንደሆነ የሚጠቅሱት አቶ ፈቃደ፣ መሻሻል ያስፈለገበት ምክንያትም አርብቶ አደሩ የተለየ አማራጭ ስለሚያስፈልገውና አዲሱ ፍኖተ ካርታ አዲስ ሃሳብ ይዞ የመጣ መሆኑን ታሳቢ በማድረግ እንዲጣጣም ለማስቻል ነው፡፡

ጅምር ሥራዎችን በተመለከተ የሚናገሩት ባለሙያው፤ የቋሚ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ስታንዳርድ፣ የተንቀሳቃሽ አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ጣቢያ ስታንዳርድ በመሠራት ላይ ይገኛል። ከዚህ በተጓዳኝም የመፈጸምና የማስፈጸም አቅም ግንባታ በዕቅድ ዝግጅት ወይም የአጭርና መካከለኛ ዕቅድ ለማዘጋጀት ሥልጠናው ለትምህርት ቤት፣ ለወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤት አመራሮች፤ በትምህርት ተቋም አመራር ክህሎት ላይ የአቅም ማጎልበቻና አዳዲስ በመሆኑ በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሥልጠና እንደሚሰጥም አቶ ፈቃደ ተናግረዋል፡፡

በተጨማሪም ከፍተኛ ባለሙያዎች ከስምንት ተሸከርካሪዎች ጋር በአራቱ ክልሎች ተመድበው እስከ ትምህርት ቤት የዘለቀ ሙያዊ ድጋፍ እያደረጉ መሆኑን የጠቀሱት ባለሙያው፣ የሩብ ዓመቱ በተመረጡ ወረዳዎችና ትምህርት ቤቶች በመገኘት የፖሊሲዎች፣ የስትራቴጂዎችና የመመሪያዎች አፈጻጸም በመገምገም ግብረ መልስ ይሰጣል ብለዋል፡፡

ምንም እንኳን የድጋፍ ሥራው አሁን ባለው ወቅታዊ ሁኔታ፣ ክልሎቹም አሁን ካሉበት ሁኔታ እንደልብ ለመንቀሳቀስ አዳጋች መሆን፣ የመሠረታዊ ልማት አለመኖር፣ የሰው ኃይል እንዲሁም የግብአት እጥረት የክትትልና ድጋፍ ሥራውን ይፈትነው እንጂ፤ ለክልሎቹ ተብሎ በሚመደበው ተጨማሪ በጀት ግብአቶችን ለማሟላት ጥረት እየተደረገ ነው፤ ነገር ግን በቂ ግን አይደሉም ይላሉ፡፡ ባለሙያ ሲያስረዱ፤ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ተማሪዎች የሚማሩት ዛፍ ጥላ ሥር ነው፤ በመሆኑም እንደዚህ ያለውን ችግር በጋራ መፍታት እንጂ ለአንድ አካል ብቻ በመተው ችግሩ የሚፈታ አይደለም፡፡

እነዚህ ችግሮች ይኑሩ እንጂ በተሰራው ሥራ ለውጦች መኖራቸውን የሚገልጹት አቶ ፈቃደ፣ ከዚህ በፊት የነበረው የትምህርት ተሳትፎ መጠን በአሁን ሰአት መሻሻል አሳይቷል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታም ልዩ ድጋፍ የሚሹት ከሌሎች ክልሎች ጋር በመገዳደር ላይ እንደሆኑ ጠቁመዋል፡፡

በቀጣይ ምን ታስቧል ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሰጡት አቶ ፈቃደ፣ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልገቻውን ክልሎች በተመለከተ ሥራውን የሚያተስተባብረው ሰላም ሚኒስቴር ሲሆን፣ ከሚኒስቴሩ ጋር ለመሥራት ታቅዷል፡፡ ከዚህ ጎን ለጎንም የክልሎቹን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ድጋፉ ተጠናክሮ ይቀጥላል፡፡ አያይዘውም ክልሎቹ ከሌሎች ክልሎች ጋር ተመጣጣኝ እድገትና የትምህርት ተሳትፎ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ራሳቸውንም እስስኪችሉ ብሎም ከድጋፍ ነጻ እስኪሆኑ ተጠናክሮ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

በመጨረሻም አቶ ፈቃደ ያስተላለፉት እንደሚያስገነዝበው፤ የትምህርቱ ዘርፍ ችግር ውስጥ ነው፡፡ ቤተሰብ ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ከመላክ ባሻገር ዘርፉን መደገፍ አለበት፡፡ ችግሩን ለመቅረፍም ሥራውን ለአንድ አካል ከመስጠት ይልቅ እያንዳንዱ ዜጋ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት፡፡

ከፐብሊክ ሰርቪስ የሰራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ጋር
በመተባበር በየ15 ቀኑ ዓርብ የሚታተም

# “በንኪኪ የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ኤሌክትሮኒክስ ካርድን ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ያደረገ ድርጅት ነው”

**- አቶ አሸናፊ ዳዕሚ**


**የቀድሞ የምክር ቤት አባልና የትራንስፖርትና ከተማ ልማት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ**

የፐብሊክ ሰርቪስ የሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት በሚሰጣቸው አገልግሎቶች በርካታ ሽልማቶችን አግኝቷል፡፡ ከዚህም ውስጥ በሀገር አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያ ጥራት ሽልማት ድርጅት ባካሄደው ውድድር የዋንጫ ተሸላሚ መሆን ችሏል፡፡ ከዚህ ሽልማት ጋር በተያያዘ ከቀድሞ የምክር ቤት አባልና የትራንስፖርትና ከተማ ልማት ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ አቶ አሸናፊ ዳዕሚ ጋር ቆይታ አድርገናል፡፡ መልካም ንባብ ይሁንልዎ፡፡

**ፐብሊክ ሰርቪስ፡- የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያሳየ ያለውን ዕድገት እንዴት አዩት?**

**አቶ አሸናፊ፡-** መንግሥት ለድርጅቱ የሠጠው ተልዕኮ ግልፅና የማያሻማ ነው፡፡ ከ2007 ዓ.ም በፊት በመዲናዋ አዲስ አበባ በተለይ በመንግሥት ሠራተኛው ፐብሊክ ሰርቫንት ብለን በምንጠራው ሠራተኛ ላይ ያጋጥም የነበረው የትራንስፖርት ችግር ከፍተኛ እንደነበረ ሁላችንም እናስታውሳለን፡፡ በዚያው ችግር ሳቢያ ሌሎች የመልካም አስተዳደር ችግሮች ይፈጠሩ ነበር:: የትራንስፖርቱ ችግር የሚወልዳቸው በተገልጋዩ ላይ ይደርስ ከነበረው ችግር በተጨማሪ ሠራተኛውም ላይ ይደርስ የነበረው እንግልት ቀላል የሚባል አይደለም መንግሥት ይህን ችግር ለመቅረፍ በማሰቡ ነው ይህ ድርጅት በአስቸኳይ እንዲቋቋም በአዋጅ ተደነገገ፡፡

ድርጅቱ በተለያዩ ጊዜያት በተደረገው ክትትል ከፍተኛውን የእርካታ ውጤት ያስመዘገበ ድርጅት ነው፡፡ ዋናው የአገልግሎት ጥራት ነው፡፡ አገልግሎት የሚሰጥ አካል በተገልጋዩ ከተመሰገነና በአገልግሎቱ እንደረካ ከተገለፀለት ስኬታማ ነው ብሎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ተሳፋሪ ሆነን



በአውቶቡሱ ተገልግለን ባናየውም እንደ ተገልጋይ ሆነን ባየናቸውና በሰበሰብናቸው መረጃዎች ድርጅቱና ተገልጋዩ በጥሩ አንድነትና የመግባባት መንፈስ እየሰሩ እንደሆነና እርካታቸውም ተጨባጭ መሆኑን አረጋግጠናል፡፡ ድርጅቱ በሚሰጠው አገልግሎት ብቻ ረክቶ የተቀመጠ አይደለም በተለያዩ ጊዜያት አዳዲስ አሠራሮችን እየቀየሰ የሄደ ለሌሎች ተቋማት አዲስ ተሞክሮን የሚሰጥ ተቋም ነው፡፡

**ፐብሊክ ሰርቪስ፡- የመንገድ ላይ የተሽከርካሪ አደጋን ለመከላከል ድርጅታችን የሚያደርገውን ማበረታታትና ቅድመ ጥንቃቄን እንዴት ታዘቡት?**

**አቶ አሸናፊ፡-** እንደ ቋሚ ኮሚቴ በሀገራችን በዓመት በመንገድ ላይ የትራፊክ አደጋ እየሞተ ያለው ሰው ቁጥር ቀላል የሚባል አይደለም፡፡ ይቅርና በሺዎች የሚቆጠር ሰው አንድም ሰው በአደጋው መሞት የለበትም ባይ ነኝ፡፡ የተጎጂው ቁጥር እጅግ መቀነስ አለበት የሚል ፅኑ እምነት አለኝ፡፡ በሰው ህይወት ላይ ድርድር የለም፡፡ ስለማይተካ ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ልንከላከለው በምንችለው አደጋ ህይወቱ ማለፍ የለበትም፡፡ ይሁን እንጂ እዚህም እዚያም አደጋዎች ይከሰታሉ። ስለዚህ ይህን መጠን መቀነስ አለብን ብለን በሰጠነው አቅጣጫ መሠረት ይህን ማረጋገጥ ያለበት የትራንስፖርት ሚኒስቴር ተጠሪ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች አገልግሎት ድርጅት ደግሞ በዚህ ሚኒስቴር ስር ያለ ተቋም ነው፡፡

መጀመሪያው ለሌላውም እንደመነሻ የሚጠቅም ተሞክሮ ድርጅቱ አደጋ መከላከል የሚጀምረው ከቅጥር ነው፡፡ ባስ ካፒቴን ሆኖ ለመቀጠር ወደ ድርጅቱ የሚመጣ ግለሰብ የኋላ ታሪኩ ምን እንደሚመስል ይጠናል፡፡ አደጋን ተከላክሎ ማሽከርከር ብቃቱና ችሎታው እንዲሁም ቀደም ሲል አደጋን የመከላከል ሁኔታው እንዴት ነበር በሚል ጥናት ይካሄዳል፡፡ ተደጋጋሚ የግጭት ታሪክ ካለው የድርጅቱ አባል አይሆንም፡፡ ይሰራበት ከነበረው ተቋም ማስረጃ ማምጣት ይጠበቅበታል፡፡ ይሄ ድርጅቱ አደጋን ተከላክሎ በማሽከርከር በሀገር አቀፍ ደረጃ ተሸላሚ እንዲሆን ካስቻሉት ማጣሪያዎች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህን ጥንቃቄ አድርገው ያለምንም አደጋ ላሽከረከሩ ባስ ካፒቴኖች ደግሞ አመታዊ የማበረታቻ ሽልማት አላቸው፡፡

ድርጅቱ በቸልተኝነት የመንገድ ላይ ተሽከርካሪ አደጋን መከላከል ሳይችል ቢሰራ አንድ አውቶቡስ ላይ የሚደርስ አደጋ ብዙ ሺህ ብር ለጥገና ያወጣ ነበር፡፡ ይህ አደጋ በተበራከተ ቁጥር ደግሞ ውጤት ያንኑ ያህል ይጨምራል። ይህ ድርጅት ደግሞ ከመንግስት ምንም አይነት ድጎማ የማያገኝ በራሱ ገቢ የሚተዳደር ነው፡፡ ለጥገና የሚያወጣው ገንዘብ ቢጨምር ኖሮ በድርጅቱ ህልውና ላይ ብዙ ፈተና ይጋረጥ ነበር፡፡ ድርጅቱ በመርህ የሚመራ በመሆኑ አደጋን ተከላክሎ በማሽከርከር ወጪውን ቀንሶ ገቢውን እያዳበረ የድርጅቱንም ሆነ የሠራተኞችን ህልውና አደጋ ላይ ሳይጥል የበለጠ በውጤት እያማረ ቀጥሏል፡፡ ይህን ሁሉም በተሞክሮነት ሊወስደው ይገባል፡፡

በተሽከርካሪዎች ላይ ደግሞ በዘመናዊ የGPS ቴክኖሎጂን ገጥሞ አውቶቡሶች የትና እንዴት ባለ ሁኔታ እያሽከረከሩ መሆናቸውን ይከታተላል፡፡ በሌላም በኩል በንኪኪ የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል ኤሌክትሮኒክስ ካርድን ለመጀመሪያ ጊዜ ተግባራዊ ያደረገ ድርጅት ነው፡፡ በብዙ ነገሮች ቀዳሚ ድርጅት ስለሆነ ደስ ይለኛል፡፡

**ፐብሊክ ሰርቪስ፡- የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት የጥራት ሽልማት ተሸላሚ ሆኗል፤ ይገባዋል ይላሉ?**

**አቶ አሸናፊ፡-** ለድርድር የሚቀርብ አይደለም፡፡ በእርግጥም ይገባዋል፡፡ በመናበብ የምንሰራው ክፍተቶችን እያረምን የመጣንበት ጉዳይ ስለነበረ ሁሉንም በቅርብ እንከታተለዋለን፡፡ ይህን በማሳካት ለዚህ ተቋም የተሰጠው ሽልማት ያንስበት ይሆናል እንጂ አይበዛበትም፡፡ ታግሎ ሠርቶ በሕዝብ ተመስክሮለት የሚሸለም ድርጅት ነበር ማየት የፈለግነው፡፡ ምኞታችንም ተሳክቶ የፐብሊክ ሰርቪስ ሠራተኞች ትራንስፖርት አገልግሎት ድርጅት እኛንም አሸልሞናል፡፡ የድርጅቱን ሽልማት ክብርና ዝና ለኛም ደርሷል፡፡ በድርጅቱ ኮርተናል፡፡